# የጄኔራል ጻድቃን ወልደተንሳይ
# “የሀገራችን ፖለቲካ እና የመፍትሄ ሀሳቦች”

አስተያየት

መንግስቱ ሙሴ

በሰሞኑ በአገራችን የሕዝብ ብሶት በቀሰቀሰው የአልገዛም ትግልን አስመልክቶ ከትጥቅ ትግሉ ዘመን ጀምረው ሕወሐትን በከፍተኛ ወታደራዊ የአመራር ቦታ የመሩ ሁለት ጀኔራሎች የመፍትሄ ሀሳብ በሚሉ አስተያየቶች ዙሪያ ሀሳቦቻቸውን ወደ ውጭ ለማሳየት ሞከረዋል። እነዚህ ግለሰቦች አነሰም በዛ በአገኙት ልምድ እና የእውቀትም መነጽር ሊደርስ የሚችለው አደጋ በተለይም በድርጅታቸው ላይ ያንዣበበውን አይቀሬ ውርደት ለማመላከት እና ልባቸው የተደፈነ ጓዶቻቸውን እንዲነቁ መቀስቀስ ለመሆኑ በሚያሳዩት ልመናም ሆነ ጥንቃቄ መረዳት ይቻላል። ሁለቱም ጽሁፎች ተጨንቀው እና ተጠበው በተለይም የታገሉለትን ድርጅት እና የታገሉለትን አላማ እየመጣ ባለው አይቀሬ ማእበል እንዳይፈርስ በመፈለግ ለመሆኑ ጽሁፎቻቸው ያሳብቃሉ።

የድህረ ምረቃ አካዳሚክ ጽሁፍ በሚመስል ሲያቀርቡ ዋና ኦዲየንሳቸው የራሳቸው የሕወሀት ሰወች በነጠላ እና ድርጅቱን በጥቅል የእናትርፍ ጩኸት መሆኑን ከዚህ በታች በዝርዝር ለማሳየት እሞክራለሁ። እነዚህን ጽሁፎች መመርመሩ ወይንም መተቸቱ ግን ምንም ፋይዳ የለውም የሚል አስተያየት እንደሚኖር በመገመት በግሌ የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሀይሎች አቅም ከትብብር አለመኖር በማጠሩ ጠላት ግዜ እንዲገዛ ብሎም የቆመለትን አላማ እንደገና መልሶ እንዲያጠናክር መሆን የለበትም ከሚል ተሀስቦ በመነሳት መሆኑን በዚህ መጣጥፍ ለማሳየት እወዳለሁ።

ጎመራው የዛሬ ሀምሳ አመት ገደማ ለዴሞክራሲ የታሰበው ትግል ሲጠነሰስ እንዲህ ብሎ ነበር።

“የአሰብከው አላማ አልሆን ብሎ ሲከሽፍ ሁኔታው ሲጠጥር፤ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር”

ጀነራል ጻድቃን ‘የሀገራችን ሁኔታና የመፍትሄ ሀሳቦች” በሚል ባሰራጩት መጣጥፍ መንደርደሪያ ሀሳብ ላይ እንዲህ ይላሉ።

“ከሃያ አምስት ዓመት ኢህአዴግ የደርግን መንግስት በጦርነት አሸንፎ የሀገራችንን ፖለቲካዊ ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ፤ ቀስ በቀስ እያደጉ የመጡ ፖለቲካዊ ችግሮች በግልፅ ጎልተው መታየት ጀምረዋል፡፡ አሁን ገዥው ፖርቲና ፖርቲው የሚመራው መንግስትም የችግሮቹን መኖር አምኖ ለመፍታት እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ መንገር ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ ይህ ሁኔታ ለማንኛውም የሀገሩን ደህንነትና ሰላም፤ ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ማህበራዊ ብልፅግና፤ ለሚመኝ ሀገር ወዳድ ዜጋ ያሳስባል፡፡ ከዚህ አንፃር የተለያዩ አስተያየቶች እየተደመጡ ነው፡”

ይህን ከላይ የተቀመጠውን የመግቢያ ሀሳብ በሕወሐት የቀድሞ መሪ እና የጦር ኤታማጆር ሹም የተጠቀሰ ሲሆን አባባሉ በትክክልም ይህ ድርጅት ያለበትን ማጥ እና መሪ አባላቱ ድርጅታቸው ከዚህ አዘቅት ሊወጣበት የሚቻለውን ጎዳና ለማሳየት ለመምከር እንደሆነ አንባቢ ይረዳዋል። እናም ጀኔራሉ ይህን መጣጥፍ ለማቅረብ የተገደዱት ለምን የሚል አስተያየት እንደሚኖር ማንም የሚገነዘበው ነው። አባባሉ ትክክል ነው ብሎ ለመቀበል ግን ብዙ ችግር አለው ምክንያቱን እንዲህ ላቅርበው። ሕወሀት መራሹ መንግስት ባለፈው ቢጋ በእርግጥም አንድ አጥኝ ግሩፕ ሰይሞ ችግር የተባሉትን በአደባባይ አውጥቶ አይተናል።

ይህን የአገሪቱን ችግር በመስክ ስራ ተሰማርተው ሕዝብን፣ አነጋግረው፣ የሚመለከታቸውን ሁሉ ቃለመጠይቅ አቅርበው የተመለሱ እና ዝርዝር መረጃወችን ያቀረቡ ሙያተኞች በየዌብ ሳይቱ ወጥቶ ተመልክተናል። ያዝርዝር ዘገባ በቀረበበት ወቅት ምን ተፈጠረ በሚያሰኝ ብዙ ዜጎች ጥያቄ አቅርበዋል። በዚያ ለእይታ በቀረበው ድራማ እንደተመለከትነው ሕወሐት በደብረጺዮን አማካኝነት የተዘረዘሩ ችግሮች የሉም ብሎ ሲከራከር። የእርሱን ሀሳብ በመጻረር መልክ የወያኔው መስራች እና የዘር ፖለቲካው ግንድ አባይ ጸሀዬ ለየት ያለ ሀሳብ ብጤ አቅርቧል። ለድራማው ማዳምቂያም ይመስላል በረከት እና ሌሎችም ድጋፍና የተለዩ ሀሳቦችን ሲያቀርቡም አስተውለናል። ድንቅ ስራ።

የዘገባው ለህዝብ እይታ እንዲቀርብ የተፈለገበት አጀንዳ ብዙም ሳይርቅ እና ሳይውል ሳያድር በኦሮሞ ወጣቶች ላይ የተሰነዘረውን ግድያ እና ተከትሎም በሽሆች ዜጎችን በእብነበለ ፍርድ ወደ እስር መወርወር አይተናል። ይህ ግድያና ፍጅት የተከናወነው የውጭ ጠላት መጥቶ ወይንም የአገሪቱ ደህንነት አደጋ ላይ ወድቆ ሳይሆን ሰላማዊ ዜጎች፣ ወጣት ተማሪወች፣ አዛውንቶች፣ እናቶች ሰላማዊ በሆነ እና ፍጹም ጨዋነት በተላበሰ የመብት ጥያቄ ይዘው አደባባይ በመውጣታቸው ነበር። ሳይውል ሳያድርም የዚያን ዘገባ ህዝብ እንዲያይ የተደረገው መሰረታዊ አላማም አንድ የፕሮፖጋንዳ ስልት ለመሆኑ የተከተለው ዘግናኝ ተግባር እና በሰላማዊ ዜጎች ሰላማዊ እና ህጋዊ ጥያቄ አቅርበው የተሰጣቸው ምላሽን አይቶ ላመዛዘነ የድራማውን ምንነት እና ለምን እንደቀረበ ለመረዳት ችለናል ማለት ነው።

ሕወሀትን ለማያውቁ ይህ ተግባር አስረጅ ይመስለኛል። ሕወሐት ከልደቱ ጀምሮ አይነታቸው ይለያዩ እንጅ ተመሳሳይ

እርምጃወችን ተራምዶ የፈጸማቸው ወንጀሎችን ማስታወሱ ጥሩ ግንዛቤ ይሰጠናል። ይህ ድርጅት ውጥረት ሲገጥመው እና መውጫው ሲጠብ ችግሩን ለመበቀል ይህን አይነት የማዘናጋት፣ የመለሳለስ እና ፍጹም የተጸጸተ በመምሰል ጊዜ ይገዛል። ያን ካለፈ በኋላ ቂመኛ፣ ሰብአዊነትን እና የኤቲክስ ጠብታም ስለሌለው አዘናግቶ እና አታሎ ግፍ ይፈጽማል። ይህን ተግባራቱን በትግራይ ሜዳ በራሱ የድርጅት አባላት ጭምር አሳይቷል። ሙሴ የተባለውን ታጋያቸውን፣ እና ዶክተርር አታክልት ቀጸላን ገድለዋል ለምሳሌ አቶ ገብረመድህን አራያ (ዲሴምበር 12 2015) ኢካዴፍ ታሓህት በአማራው የፈጸመው ወንጀል በሚል ባስነበቡን መጣጥፍ የዚህን አጥፊ ድርጅት ሲወጠር የመላላት ባህርያት እና በቀናው ጊዜ ደግሞ አዘናግቶ የሚወስዳቸውን ፋሽስታዊ ወንጀሎች በጥሩ መልክ አቅርበው አስነብበውናል። ሕወሀት በትግራይ እርሱን በሚቀናቀን አንድ የትግራይ ድርጅት የእንታረቅ ሀሳብ አቅርቦ እና ተደራድሮ ለስምምነት ከደረሰ በኋላ በቡድኑ አመራር በተኙበት የወሰደው የፍጅት ተግባርም የዚሁ ድርጅት አዘናግቶ የመግደል ታሪካዊ እድገቱ መሆኑን የአመራሩ አባል አቶ ገብረመድህን አርያ በዝርዝር አስረድተዋል።

ይህን የመሰሉ ተግባራትን በሚፈጽምበት ሁሉ የእቅዱ ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን በመሪነት ከሰሩት አባላት አንዱ ጻድቃን ወልደተንሳይ ነበሩ። ለማሳየት የሚሞክሩትም ይኸውን የድርጅቱን ታክቲካል የሆኑ እርምጃወች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው የሆነውን ሲጠቃ የማዘናጋት መላውን ነው ብል የኔን ሀሳብ ማፍረሻ አመክንዮ ሊቀርብ ግን እንደማይችል እሞግታለሁ። አንድ ነገር ግን ግልጽ መሆን ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በጥቅል እና ዛሬ በተለያዩ አካባቢወች የተነሱ የሙብት፣ የነጻነት ጥያቄወች ግን ሕዝብን በመግደል ያለመቆማቸውን በተግባር እያሳዩን ነው።

ወያኔው ምርጫ 97 በግድያና አፈና ካጠናቀቀ በኋላ ያለምንም ተቀናቃኝ። አለምን ባስደመመ እንዴውም ደጋፊወቹ እነ ሱዛን ራይት የፕሬዜዳንቱ የደህንነት አማካሪ ሹም ባንድ ወቅት አሁን የተባበሩት መንግስታት አሜሪካን ወኪል ቱግ ባለሳቅ የሰጡትን የፐረስ ምልልስም አይተን የታዘብነው ነው። እናም ወያኔው በ 100% ምርጫ ወሰድሁ እያለ ባፌዘበት ማግስት ነው የኦሮሞ ወጣቶች ሰላማዊ ተጋድሎ በአመጽ ምላሽ የሰጠው። ዛሬ ያም እንደቀጠለ ሆኖ በሰሜናዊ የትግራይ አዋሳኝ በሆነው የሰሜን ጎንደር የወልቃይት፣ የጸገዴ፣ የጸለምት ሕዝብ የማንነት ጥያቄ ለሦስት አስርት አመታት የጠፋ መስሎ ቢቆይም ከምንግዜውም በላይ ገዝፎ መውጣት። በጎንደር ሕዝብ የሙብት ጥያቄ እና የማንነት ጥያቄውን ደግፎ መነሳት ወያኔዋ ድርጅት ልትመክተው እስኪሳናት ቀጣይ መሆኑን የተረዱት አበበ ተክለ ሀይማኖት እና ጻድቃን ወልደተንሳይ የድርጅታቸው ነፍሰገዳዮች የእረገብ በሉ ምሁራዊ አስተያየት የሚጠበቅም ነው። ጻድቃን ወረድ ብለውም በመግቢያቸው እንዲህ ይላሉ።

"ሃገራችን በአሁኑ ግዜ እጅግ ባልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ነው የምትገኘው የሚል እምነት አለኝ። መንግስት የሚያወጣቸው መግለጫዎችም ይህንኑ ያመላክታሉ። ሰፊ የመልካም አስተዳደር እጦት እንዳለ፣ በግልባጩም ብልሹ አስተዳደር በተለያዩ መንግስታዊ መዋቅሮች እንደተስፋፋ፣ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ከፍተኛ እንደሆነ፣ የመንግስት ገንዘብና ንብረት ብክነት በሰፋት እንደሚታይ፣ ትልቅ ተስፋ የተጣለባቸው ሃገራዊ ፕሮጀክቶች በግዝያቸው እንደማይጠናቀቁ ይህ ደግሞ አገሪቱን ለከፍተኛ ችግር እያጋለጣት እንደሆነ ይገለፃል። በተለያዩ የሃገራችን አካባቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች (የማንነት ጥያቄ፣ የኢኮኖሚ ተተቃሚነት ጥያቄ፣ የፍትሕ መጓደልና፣ የመልካም አስተዳደር እጦት ወዘተ) በኦሮምያ፣ በደቡብ ህዝቦች፣ በአማራ፣ በትግራይ የህዝብ መነሳሳትና መንግስት ጥያቄዎቹን እንዲፈታላቸው በሰላማዊ መንገድ እየጠየቁ ይገኛሉ፡፡"

ትክክል ነው። ጀኔራሉ ከላይ ይህን በሕዝብ እና በአገር ላይ እየደረሰ ያለውን በደል እና ወንጀል ግልጽ በሆነ መልክ አስቀምጠውታል። በእርግጥም ማንም ህሊና ያለው የሚስተው ጉዳይም አይደለም። ይህ ግፍ ፈጻሚው ቡድን ደግሞ ከህዳጣኑ ክፍል የመጣ ሆኖ ሳለ በአገራችን ታሪክ ዘርን ተመርኩዞ በሌሎች ላይ አይን ያወጣ በደል የፈጸመ ተወዳዳሪ የዚህን ድርጅት መሰል ገፈኛ መንግስት አልነበረም፤ የለም። ለምሳሌ የወያኔ ባለስልጣናት በተለይም ወታደራዊ ማ'እረግ ያላቸው በቢሊዮን የሚቆጠር ንብረት በአገሪቱ አፍርተዋል። ይህ ንብረት በማንኛውም መልክ የእነርሱ እንዳልሆነ ሁሉም የሚያውቁት ጉዳይ ነው። በአዲስ አበባ እና በሌሎች ታላላቅ ከተሞች ሕዝቡን በተለያየ ምክንያቶች አፈናቅለው ለእነርሱ ቪላወች እና ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ሰርተዋል።

ለዘመድ አዝማዳቸውም ከእነርሱው አልፈው የሚችሉትን አድርገዋል። እነርሱን የተጠጉ ሁሉ ከብረዋል። ይህ የሚሆነው 14 ሚሊዮን ሕዝብ በተራበበት አገር፤ የበረንዳ አዳሪው ቁጥር እቤት ቀልሶ ከሚኖረው እኩል በሆነበት አገር መሆኑ ነው። እናም የቀድሞው የጦር ሀይሎች (የወያኔ) አዛዥ በትክክል ዘግበውታል። እናስ ምን ማድረግ አለብን የሚለው ላይ አሁንም ድፍረት የሚጠይቅ ከዘረኝነት የጸዳ መልስ ይፈልጋል። ለመሆኑ መልካም አስተዳደር ማለት ምን ማለት ነው? ይህንን ቃል በሁሉም የዚህ ስርአት ሰወች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይናገሩታል። በተግባር ደግሞ ሲተረጉሙት አይታይም። ጀኔራሉ እንዳሉት የመልካም አስተዳደር እጦት ዜጎችን አገራቸውን እየለቀቁ እንዲሰደዱ አድርጓል። ዜጎች ለምን አሰባችሁ ተብለው ወህኒ ሲወርዱም እያየን ነው። ወህኒወች በወንጀለኞች ሳይሆን ለሙብት ተከራካሪ ዜጎች እየተሞሉ ነው።

ጋዜጠኞች የታዘባችሁትን ለምን በጽሁፍ አሰፈራችሁ ተብለው እስር ወርደዋል። በአለም አቀፍ ህግ የተከለከለውን የማሰቃያ ዘዴ ይህ መንግስት በየቀኑ እና በየጉራንጉሩ ይጠቀማል። እናም ዜጎች አካላ ስንኩል ወይንም የአ'እምሮ ችግርም እንዲደርስባቸው ሆኖአል። ለህግ ተገዥ ያልሆኑ የማያነቡ እና የማይጽፉ ሰወች ተመርጠው ህግ አስከባሪነትን ያክል ከባድ ሀላፊነት በመውሰዳቸው ዜጋን እንደጠላት ተመልክተው የተሸከሙት መሳሪያ ሰላማዊ ሰውን መግደል ፍትህዊነት፣ ታማኝነት አድርገው ስለሚቆጥሩ ዜጎች ደማቸው እንደውሻ ደም በየቦታው ይፈሳል።

እናም ለዚህ ሁሉ ብልሹ አስተዳደር (የጀኔራሉ አባባል ነው) ወንጀል ብንለው ሲያንስ ነው እና ተጠያቂው ማን ነው? በህዝብ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ማመን እና አምኖ ማስቆም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እንደሚመስለኝ ግን ወያኔ የተባለው

አረመኔ ቡድን ይህንም ለማን ሊያላክክ ፈልጎ እንደሚናገረው ባናውቅም የወንጀሉ ቀንደኛ አስተናጋጅ ከእርሱ የራቀ እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ አውቆታል። እናም መፍትሄው ትግል ነው። የሚቆመውም የወንጀሉ ምንጭ የሆነውን ወንጀለኛ በማስወገድ ነው ብሎ ጀምሮታል። ጻድቃን ትክክል ናቸው ገዝፎ የመጣ ችግር የመጨረሻው የሁሉም አንባ ገነኖች ፍጻሜን አንዳቀረበ ሁሉ የወያኔው እና ተከታዮቹም እጣ ፈንታ ይኸው እንደሚሆን የሞሀመድ ጋዳፊን፣ ወይንም የሙባረክን ቀን እነርሱም እንደሚጋሩ መጠራጠር አይቻልም። መንገዶች ሁሉ እየወሰዱን ያለው ወደዚያው ነውና።

ጻድቃን የዚህ የመልካም አስተዳደር መጥፋት መሰረታዊ ናቸው ብለው ያቀረቡት ሦስት አበይት ጉዳዮችን ነው። እነርሱም 1) ከኦነግ ጋር የነበረውን ቅራኔ አፈታት 2) በወያኔ ውስጥ የተፈጠረው ልዩነት እና ቅራኔውን የተቋጨበት መልክ 3) ምርጫ 97 ን ተከትሎ ወያኔ መራሹ መንግስት የተጠቀመበት የአፈታት መልክ መሆናቸውን ያስቀምጡ እና ዝርዝሩን እንዲህ ይጀምራሉ።

“የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ የሽግግር መንግስቱ ቻርተር በመሰረቱ በኢህአዴግና በኦነግ (የኦሮሞ ነፃነት ግንባር) መካከል በተደረሰበት ስምምነት ፀደቀ፤ ጊዝያዊ የሽግ ግር መንግስትም በዚህው ስምምነት መሰረት ተመሰረተ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በኢህአዴግና በኦነግ በተፈጠረው አለመግባባት ኦነግ ከመንግስት ወጣ፣ ውግያዎቹም ተካሄዱ። በዚህ ሂደት ጥፋቱ የማን ነበር የሚለውን ጥያቄ ለታሪክ እንተወውና ይህ ክስተት ግን በኢትዮጵያ ሊመሰረት ይችል የነበረውን የሃይል ሚዛን መሰረት ያደረገ ውስጣዊ የቁጥጥርና የተጠያቂነትን አሰራር ለመመስረት የሚያስችል የነበረ እድል እንድናጣ በማድረግ የዴሞክራስያዊ ስርዓት ግንባታውን ሂደት በከፍተኛ ደረጃ ጎድቷል የሚል እምነት አለኝ። ኦነግ የራሱ ችግሮችና ስህተቶች የነበሩት ቢሆንም በወቅቱ ግን የኦሮሞ ህዝብ ፍላጎትና ስሜት የሚያንፀባርቅ የፖለቲካ ሃይል ነበር።”

ይህች ከላይ በሁለተኛ እረድፍ ምክንያት ብለው ያስቀመጧትን ለታሪክ ትቶ በማለፍ ጉዳይን በተመለከተ ትንሽ ልበል። በመሰረቱ ይህች አጥፊ ድርጅት ስትመሰረት ቅራኔን ለመፍታት የምትጠቀምበትን ዘዴ ጠቁሚዓለሁ። ወያኔ ከፍጥረት እስካሁን በማለዘብ እና በማዘናጋት ተቀናቃኝን በሀይል ማስወገድን መሰረታዊ አላማ የተከተለ ድርጅት ነው። ለዚህ አቶ ገብረመድህን አራያ በወልቃይት፣ በጸለምት እና በሌሎች ሁሉ የፍጅት ዘመቻ የአይን ምስክርነታቸውን በ (2015) በኢካዴፍ በአስነበቡን መጣትፍ መመልከት ብቻ በቂ ማስረጃ ነው። ይህን ዘዴ ደግሞ እንደአንድ ጦር መሪ ጻድቃንም ተሳታፊ እንደነበሩ የአቶ ገብረመድህን አራያ ጽሁፍ ያስረዳናል። ሌላው ወያኔ ኢሕአፓን ከትግራይ እንዲወጣ የተጠቀመችበት ሁሉ ስልት ይኸው የማጥፋትን ስልት እንደነበር ድርጅቱ በተደጋጋሚ ባወጣቸው ጽሁፎቹ ገልጿል። ወያኔ በኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ላይ ሁሉ ነበር የዘመተችው። ኢድዩ ይባል የነበረውን ድርጅትም መጀመሪያ የእንደራደር ተማጽኖ በመላክ ድርድሩ ሳይቋጭ ቦታና ግዜ መርጣ በተመሳሳይ መልክ ድንገተኛ አደጋ በመጣል ብዙ የድርጅቱን ሰወች ገድላ ከትግራይ አስወጣች። እናም

እስኪ የጻድቃንን ከኦነግ ጋር የተቋጨውን ስህተት ብለን እንቀበል እና እንመልከተው። ለመሆኑ የሽግግር መንግስት ተብሎ ከጅምሩ ሲመሰረት አይደለም ትልቁ ስህተት የተሰራው? ያየሽግግር መንግስት የተባለውስ አካል የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታ ያገኘ ነበር? ወይንስ የሽግግር ተብሎ የተሰየመው አካል ሁሉንም ሀይሎች ያካተተ ነበር ወይ? እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄወች ጻድቃን እንደማይመልሷቸው ከጅምሩ አመላካች ነው። በመሰረቱ ኦነግንም በሽግግር መንግስቱ ለማካተት የተፈለገው ያው ይህች ድርጅት ስትመሰረት የተጓዘችበት ጎዳና ሁሉ በመነጠል እና በመመንጠር ስልት የተቃኘ ስለነበር ኦነግንም ለጊዜው በኦሮምኛ ተናጋሪ ወገን ህጋዊ ነትን ለመላበስ እንጅ ገና ከጅምሩ እቅዱ ግዜን ጠብቆ የማስወገድ ስልት እንደነበር ግልጽ ነው። ለዚህም ነው ኢሓፓን፣ ኢዴዩን ብሎም የብዙ ድርጅቶች ስብስብ የነበረውን ኢዴሐቅን በማግለል እነዚህ ስብስቦች ደግሞ ብዙሀኑን ዜጋ የሚወክሉ ግዙፍ ሀይላት ሆነው ሳለ እነርሱን በማግለል ኦነግን አናጥሎ ለመምታት በተሰላ ስሌት ነበር ሽግግር ተብሎ የተጀመረው። እናም ጻድቃን አሁንም የመፍትሄ ሀሳብ ብለው ባቀረቡት ጽሁፋቸው ይሁነኝ ብለው ይህን የድርጅታቸውን ያውም እርሳቸው በግልጽ የሚያውቁትን፣ የመከሩበትን ጉዳይ ዘለው ለማሳየት ይሞክራሉ። ለሁሉም ጅማሮው መልካም ቢሆንም ከመሸ መሆኑ ደግሞ ያሳስባል።

በይበልጥም በዚህች አገር ስህተትን አምኖና ተቀብሎ ንስሀ ተገቢ ሆኖ እያለ። የሁሉም ወንጀሎች ተካፋይ እንዲሁ የእራስን ደዌ ሳያጸዱ ወደአደባባይ እየወጡ ለመምከር መሞከሩም ተአማኒነትን አይሰጥም። ላለፉት አርባ አመታት እና ከዚያም በላይ በሀገር እና በህዝብ ለደረሰው ጉዳት ድርሻ አለመውሰድ የተለመደ ሆኖ። ወንጀል የሰሩ። የሰው ቤት ያፈረሱ። አገር የናዱ እና ያስገነጠሉ። በብዙ ሽህ ዜጎች ላይ እርምጃ ወስደው ያስጨረሱ የጨረሱ ሁሉ ሀላፊነት ሳይወስዱ አንዱ በሌላው እየተተካ ቀጥለናል።ይህ ለተተኪ ትውልድም ሆነ ለታሪክ መልካም ነገር አይደለም። ጉዳት፣ መጎዳዳት እና አገርን መቀመቅ መስደዱም እንደወንዝ ጅረት ቀጥሏል ይቀጥላልም። ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ ዘመን ሲያልቅ የሆነው የእርቅ እና የሰላም ድርድር ማድረግ ነበር።

ይህ አሮጌውን ስርአት ወርውሮ አዲሱን በአንጹህ መጀመር ስለነበር። ወንጀል የሰሩ ሁሉ ንስሀ ገብተው ለሰሩትም ሀላፊነት ወስደው ነው እንደአዲስ እርቁን እና ህብረተሰቡን የተቀላቀሉት። በእኛ አገር ገዳይ አስታራቂ። ገዳይ መካሪ እና ዘካሪ ሲሆን ይህ አዲስ ባይሆም ደግመን ደጋግመን ስናይ፣ ስንታዘብ ግን እንዴት ዝም ልንል ያስችለናል? እስኪ ልቀጥል ጀኔራሉ እንደሁለተኛ ዋነኛ እንቅፋት ለተሰራው ጥፋት ሁሉ የቆጠሩትን በድርጅታቸው ውስጥ የተፈጠረውን ልዩነት ነው። እናም እንዲህ ይሉናል።

“ከኤርትራው ጦርነት በኋላ በ 1993 ዓ.ም በህወሃት ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈልና ይህ መከፋፈል የተፈታበት

መንገድ ሌላ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ ከፍተኛ ጥቁር ጠባሳ ያስቀመጠ ፖለቲካዊ ክስተት ነበር። የክፍፍሉ አጀንዳዎች ምንምን ነበሩ፣ የትኛው ወገን ትክክለኛ፣ የትኛውስ ስህተት ነበር የሚለው አሁንም ለታሪክ እተወዋለሁ። አጀንዳው ምን ይሁን ምን መከፋፈሉን ለመፍታት የተወሰደው እርምጃ የድርጅቱን ሕገ ደምብ የጣሰ፣ ድርጅት ፈረሰ በሚል ማስፈራርያ የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ህይወትና አሰራርን በመጣስ ገደል ውስጥ የከተተ ክስተት ነበር። ጉዳዩ በህወሃት ውስጥ የነበሩ በፖለቲካው ከፍተኛ ሚዛን የነበራቸው ሰዎች ለምን ወጡ አይደለም። አወጣጣቸው የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ ያልተከተለ፣ የተወሰነ ሃይል ሌላውን ክፍል ከውስጠ ፓርቲ አሰራር ውጪ የፀጥታ ሃይሎች ተጠቅሞ ያባረረበት አሰራር ነበር።"

እንደሚገባኝ እና ከላይ እንደገለጽሁት ይህች ድርጅት አንድም ጊዜ ዴሞክራሲ የሚባል ኖሯትም ሆነ ሞክራው አለማወቋን ለማሳየት ሞክሪያለሁ። የተጓዘችበት መንገድ በማሰገድ ፖለቲካ የተካነች። አጥቂ እስካልሆነች የማትመለስ፡ ከዘመናዊ የፖለቲካ እምነት ውጭ እና ቂመኛ እንደሆነች ግን ዛሬ ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው የአደባባይ ሚስጥር ነው። እናም የመለስ በለስ ቀንቶት ተቀናቃኞቹን ቢያስወግድ የነበረ እና የቆየ የድርጅቷ የውስጥ ባህል እንጅ አዲስ እነቱ ለጀኔራሉ እና ለጓደኞቻቸው ይሆን ይሆናል። ምክንያቱም ግልጽ ነው።

መቸም በዳይ በራሱ በደል ሲደርስ ሊያምን ይሳነዋል። ለዚህም ነው በይበልጥም ለአገር ተብሎ የሚመከር የትኛውም ስብሰብ ወይንም ውይይት ሁሉ ሚዛን እንዲኖረው ይገባል የሚባለው። ሚዛኑን ካጣ በአገር እና በህዝብ የሚደርሰው ጉዳት ዋጋው ብዙ ስለሚሆን ማለት ነው። ወያኔን ደደቢት መስርተው የነጻ አውጭ ብለው ሰይመው ከተነሱ ማግስት ጀምሮ አንድም ቀን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግ እሳቦት ኖሯቸው አያውቅም። አፈጣጠሯም ለድግ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለእድገት፣ ለብልጽግና እና ለሰላም አልነበረም አይደለም። አጀንዳዋን ለመፈጸም ግን የምትጠቀምበት አካሄድ ኋላም በውስጧ ለተነሳው የሀሳብ ልዩነት የተጠቀመችበትን የማስወገድ እና ድጦ የማለፍ ፖለቲካ ነበር። አጥቂው ክፍል ያንኑ የጋራ ስራቸውን ተገልግሎበታል ማለት ነው። እናም የእነርሱ መለያየት፣ መጠፋፋትም ሆነ መወጋገድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፋይዳ አልነበረውም ወይንም ጥቅምም ጉዳትም የለውም።

"ቀድሞ ነበር እንጅ መጥኖ መደቆስ፤ አሁን ምን ያደርጋል ወጭት ጥዶ ማልቀስ"

ጀኔራሉ ይህን አሁን በአገር እና ህዝብ ላይ እየደረሰ ላለው ጉዳት እንደ አንድ ምክንያት ማቅረባቸው "ፍየል ወዲህ፤ ቅዝምዝም ወዲያ" እንዲሉ የተራራቀ አመክንዮሽ ነው። ይህ የቀረበው ምክንያት ለሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዚህች ድርጅት ጨርሶ መጥፋት ለአርባ አመታት ትግል ምክንያት ለሆነው የሕዝብ ጥያቄ ፈች ይሆን ነበር ባይ ነው። ዛሬም በመላ አገሪቱ ቦግ እልም እያለ የቀጠለው ትግል ይዋል ይደር እንጅ ፍጹም ፀረ ሕዝብ የሆነችውን ጎጠኛዋን ሕወሐትን ለማጥፋት እንደማይመለስ ማወቁ ተገቢ ነበር። መማር መልካም ነው። አስቀድሞ ንገሮችን ማየትን። ክፉ ከደግ የመለየትን ጸጋ ያጎናጽፋል። ጻድቃን ይህን የመጨረሻው መጀመሪያ መሆኑን ተረድተዋል። ለዚህ መፍትሄ መስጠትና አዲስ ሀሳብ ማቅረብ አይደለም፣ መገመት እንኳን የቻሉ አይመስለኝም። አለያም የማደናቆር ወይንም ይህችውን የጥፋት ሐይል ለማደስ ተቃውሞን ለማርገብ መላ እያፈላለጉ አስመስሎባቸዋል። ወያኔም ሆነች የእርሷ ፍጡራን የሆኑት የዴሞክራሲ ምንነትን አይደለም ስሙን የሚያውቁ አይመስሉም:: ግን ጻድቃን እንዲህ ይሉናል።

"ከዚህ ጊዜ በኋላ የህወሃት/ኢህአዴግ ባህሪይ የነበረውና የድርጅቱን ዴምክራሲያዊ ባህርይ መጠበቅ ላይ ቀላል ያልሆነ አስተዋፅዖ የነበረው የጋራ አሰራር መርህ (collective Leadership) አንድ ሰው የፈለገውን በሚወስንበት አሰራር ተተካ፡፡ በፓርቲው ውስጥና በሰራዊት ከትጥቅ ትግሉ ወቅት ጀምረው በትግል የቆዩ ነባር ካድሬዎችና የሰራዊት አባላት የራሳቸው ስብእናና አቋም ያላቸው እየተመነጠሩ ተባረሩ ወይም ራሳቸውን አገለሉ፡፡ እንደኔ አመለካከት ይህ ክስተት ሌላው የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ ገድል በመከተት የዴሞክራሲ ምህዳሩን ያጠበበ ፖለቲካዊ ክስተት ነበር፤ አሁን ለደረስንበት ሁኔታም ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል"

ጸሃፊው በሕወሐት አመራር እንደመቆየታቸው አሰራራቸው የጋራ አመራር ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት በእኩዮች መካከል መስመር ሳይተላለፉ ሰርተው ሊሆን ይችላል። አቶ ገብረመድህን አራያ እንደነገሩንም መስራት ብቻ አይደለም ሕዝብ እና አገር መቀመቅ የከተተ ብዙ ተግባራትን ጻድቃን የጋራ አመራር እያሉ የሚጠሩት ክፍል ፈጽሟል። የወልቃይት፣ የጸገዴ፣ የፀለምት ሕዝብ የጉድጓድ እስር እና እርሸናም በጋራ ለመወሰኑ የጋራ ወንጀል መሆኑንም እናውቃለን ትክክል ነው። ግን የወያኔ አመራር ዴሞክራሲያዊ ነበር። እኛ ከለቀቅን በኋላ ተለወጠ አባባል ያዋጁን በጆሮ እንዳይሆን።

ወያኔ ከፍጥረቷ ጀምሮ ጸረ ዴሞክራሲ፣ ጸረ ሕዝብ እንደነበረች እና ያንን የትውልድ ባህርይ ተሸክማ ዛሬም ሕዝብ እና አገር እየገደለች ለመሆኑ አይደለም ኢትዮጵያውያን የውጭ ደጋፊወቿ መክረውበታል። ያውቁታልም። የሔርማን ኮህንን የኢሳት ቃለ ምልልስ ማዳመጥ በቂ ግንዛቤ ይሰጣል። የስርአቱ አራማጆች ስለእነርሱ የሚባለውን ላይሰሙ ይችላሉ። ጀሮ ለእራሱ ባእድ ነው ይላሉ አበው። ጸሀፊው መንገድ ቆመው ሁለት ሶስት ሳምፐል መውሰድ ይችሉ ነበር ይህን አይነት ብዙ አዋቂ የሚያነበው ጽሁፍ አውጥቶ ተጨፈኑን ምን አመጣው። እንዳልሁት እየመጣ ያለውን ክፉ ቀን ተመልክቶ መታረም ይገባል ማለት ተገቢ የሰው ልጅ ስራ ነው። የቀደመ ወንጀልን አልተደረገም። እኛ በነበርንበት ግዜ ዴሞክራሲ ሞልቶ ተርፎ ነበር የሚለው አባባል ግን ልክ አይሆንም። ፋሽስታዊነቱም ሆነ ጸረ ዴሞክራሲነት ወይንም ዘረኝነቱ ሁሉ የአንድ ወይንም የሁለት ግለሰቦች ሳይሆን የድርጅቷ አፈጣጠር እና መሰረታዊ አቋም ነው። ያንን ደግሞ ጻድቃን እንደአንድ መሪ ይጋሩታል። በአገር እና በህዝብ የተሰሩ ወንጀሎች ሁሉ እንደጸሀፊው የእምነት ቃል የጋራ አመራሩ እና የአንባ ገነኑ ዘረኛ ቡድን ውጤቶች ናቸው።

እስኪ ሶስተኛ እና ዋነኛ ያሉትን እንመልከት“ከዚህ ከ 1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር ተያይዞ የሚነሳ አንድ መጥፎ ጠባሳ አለ፡፡ ይኸውም በምርጫ እኔ አሸንፌያለሁ እኔ አሸንፌያለሁ በሚል የተሟሟቀ ክርክር ውስጥ ቅንጅት በግልፅ በአደባባይ ዘረኛ የሆነ ፕሮፖጋንዳ ማስፋፋት ጀመረ፡፡ ውስጥ ለውስጥ በተደራጁ ሃይሎችም ይህንን ፀረ የትግራይ ተወላጆች የሆነውን ዘመቻቸውን አስፋፋው ይህንን ዘረኛ አስተሳሰባቸውን በተገቢው መንገድ አላስተባበሉም፡፡ ኢህአዴግ ደግሞ ይህንን አድሃሪ ዘረኛ ፕሮፖጋንዳ አስተጋባው ሊፈጁህ ነው፡፡ የሩዋንዳ ዓይነት መገዳደል ይከሰታል ማለት ጀመረ፡፡ ይህ ሁኔታ ሕብረተሰቡ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በትክክለኛ መንገድ ሳይሆን የፖለቲካ ሃላፊዎች በሚፈልጉት መንገድ እንዲያይ አደረገው፡፡ ቢያንስ የትግራይ ተወላጅ የሆነውን አስደነገጠው፡፡ ይህ ለፀረ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ምሽጋቻውን ለማጠናከር ጠቀማቸው፡፡ ይህ መጥፎ የፖለቲካ ጨዋታ የፈጠረው ጠባሳ እስከ አሁንም ድረስ ሙሉ በሙሉ አልሻረም፡፡ አሁንም እንደመጠቀሚያ መሳሪያ ይነሳል፡፡”

መለስ ዜናዊም ይህንኑ ነበር ያለን። ሰላማዊ ዜጋን፣ ድምጻችን ይከበር ያሉ ወጣቶችን፣ በአደባባይ ወያኔ የኢጋዚ ወታደር አሰልፎ የገደለውም ለዚሁ ነው። በመሰረቱ ይህ የሀሰት ክስ እና የህዝብን ምርጫ መቀማት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ዘረኝነት በሕወሐት እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘረኝነትን አያውቅም። ቅንጅት የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ስብስብ ነበር። ኢትዮጵያዊ መልክም ስለነበረው በምርጫም አሸናፊ ለመሆን ቻለ። ጻድቃን እንደምክንያት ያቀረቡት ሦስተኛው እና ዋነኛው ጉዳይ ይህ መሆኑ ነው።

ጻድቃን ይህን ከላይ የዘረዘሩትን ምክንያቶች እና መንስኤወች ከዘረዘሩ በኋላ የመፍትሄ ሀሳብም አቅርበዋል። እስኪ አንድ ምሳሌ ላቅርብ። ጸሀፊውንም መልካም ማሰባቸውን ልቀበል። አንድ ዶክተር መጀመሪያ የበሽተኛውን ህመም ምን እንደሆነ ለማወቅ ይመረምራል። ምርመራው ለተለያየ በሽታ የተለያየ መድሀኒት ስለሚያስፈልግ ነው። እናም ለወባ በሽታ የጉንፋን መድሀኒት ቢታዘዝ በሽተኛ እንደማይድን እሙን ነው። በዚህ በምንሰጣቸውም ትንታኔወች ለኢትዮጵያ ችግር የችግሩን መንሰኤ ካላወቅን መፍትሄውን ለማፈላለግ እንደሚቸግረን ማወቅ ያስፈልጋል።

ጻድቃን ከላይ በዘረዘሩት ምክንያት አስተዳደር ተበላሸ ይሉናል። ሞጋቾቻቸው ደግሞ አይደለም ለብልሽቱ መንሰኤ እራሱ ድርጅቱ እና ከስር መሰረቱ የድርጅቱ አላማወች ናቸው ይላሉ። ጻድቃን ችግሩ ህገመንግስቱን አለመከተል ነው ይሉናል። ሞጋች ህገመንግስቱ እራሱን የቻለ ዋናው ችግር ነው ይላሉ። ወያኔ እራሱ ዘረኝነትን ጎትቶ ያመጣ ዘረኛ ድርጅት ስለሆነ በየቦታው እና በአራቱም ማ’እዘናት የምናየው እርሱ የዘራው መህርን ማጨድ መጀመሩ ነው እንላለን። እናም ጻድቃን ግን መፍትሄ የሚሉት ጋር ብዙ የተራራቁ መሆናቸው ላሳሰባቸው እወዳለሁ። ችግሩ ጋርም አይተዋወቁም ባይ ነኝ።
ለዚህች አገር ችግር አንባ ገነን መንግስታት እና የአንባ ገነን መንግስታት ስረመሰረት፣ አቋምና አላማቸው ነው። በተለይም ወያኔ እራሷ ያጠመደችው ወጥመድ ውስጥ እየገባች ነው እናም አገርን ይጎዳል ባይ ነኝ።

ጸሀፊው scenario (ቢሆን) ብለው ያሉትን ትክክል ነው። አገራችን ብዙ ቋሚ ጠላቶች ያሏት አገር ናት። ለሕወሐትም መፈጠር፣ እድገት እና እዚህ መድረስ ብዙውን ድርሻ ወሳጅ ምክንያቶችም የአገሪቱ ቋሚ ባላንጣወች ናቸው። እናም በውስጥ የሚነሳ ብጥብጥ አገሪቱን የት ሊያደርሳት እንደሚችል መገመት ከባድ ነው። ግን አሁንም መታወቅ ያለበት የዚህ ብጥብጥ ዋነኛ ተዋናይ እራሷ ወያኔዋ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል።
ለሁሉም ሰው አንዴ ይታለላል ሁለት ሦስት ጊዜ ግን ከደገመ የጤና ጉድለት ይሆናል።
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!